# የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ችግር አሳሳቢነት

### መግቢያ

በኢትዮጵያ አብዛኞቹ በሽታዎች ተላላፊ ሲሆኑ እነዚህን ለማከምና ለመከላከል የፀ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች በከፍተኛ ደረጃ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከልና ማከም በመቻላቸው ምክንያት በስፋት እና በአብዛኛው አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓቸዋል። አግባብ ያልሆነ የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች አጠቃቀም ደግሞ መድኃኒቶች በበሽታ አምጪ ተኅዋስያን በቀላሉ እንዲለመዱ ያደርጋቸዋል።

### የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ የሚያስከትሉት ችግሮች

የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ በሰዎች ጤና ላይ ከፍተኛ ችግር ያስከትላሉ። በሽታ አምጪ ጀርሞች በቀላሉ በመድኃኒት መወገድ ባለመቻላቸው ሕሙማን ለተጨማሪ ሕመምና ወጪ ይዳርጋሉ፤የጎንዮሽ ጉዳታቸው ደግሞ ከፍ ያለ መድኃኒቶችን ለመውሰድ እንገደዳለን፣ በተመላላሽ ሕክምና መታከም የሚችሉ ሕሙሞችን ሆስፒታል ተኝቶ መታከም ሊኖርብን ይችላል። በመጨረሻም በሽታ አምጪ ጀርሞች ገበያ ላይ ባሉ መድኃኒቶች ማከም ባለመቻሉ ለሞት ሊዳረጉ ይችላሉ።

የጸረ-ተኅዋሲያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ዓለማችን ከሚያሰጓት ትልልቅ ችግሮች መካከል የሚጠቀስ ነው። በሰው በእንስሳትና በአካባቢ ጤና እንዲሁም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ችግር እያስከተለ ያለና በዚህ ችግር ምክንያት በየዓመቱ ከ750ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች የሚሞቱ ሲሆን ችግሩን ለመቀነስ እርምጃ ካልተወሰደ እ.ኤ.አ በ2050 ወደ 10 ሚሊየን የሚጠጉ ሰዎች ይሞታሉ ተብሎ ይገመታል። ችግሩ ከዚህም ባለፈ በአጠቃላይ የዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከ2 እስከ 3 በመቶ ማለትም ወደ 10 ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ እንደሚያስከትልም ይገመታል።

ይህ ችግር በሁሉም የዓለም ክፍል የሚታይ ቢሆንም እንደ ሃገራችን ባሉ በቂ የሕክምና መስጫ ተቋማት በሌሉበት፣ በቂ የንጹህ ውሃ አቅርቦት በሌለበትና ውስን ሀብት ባላቸው ታዳጊ አገራት የችግሩ አሳሳቢነት ጎልቶ ይታያል። የችግሩን አሳሳቢነት በጥቂቱ ለመጠቆም ያህል የቲቢ፣ ኤች.አይ.ቪ. እና የወባ መድኃኒቶች እንደዚሁም በስፋት በምንጠቀምባቸው በሌሎች የጸረ- ተኅዋስያን መድሃኒቶች ላይ እየተከሰተ ያለው በጀርሞች መለመድ ችግር ግልጽ ማሳያ ነው። ይህ ችግር በእንስሳት ጤና ላይም በስፋት ጎልቶ ይታያል።

### ለፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ዋና ዋና ምክንያቶች

የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶችን ያለ ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ መውሰድ፣የታዘዘን የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒት ማቋረጥ፣ መጠኑን በመቀነስና በመጨመር መውሰድ እንዲሁም የመውሰጃ ሰዓትን ማዛባት፤የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶችን ከሌላ ሰው ተውሶ መውሰድ፤ያለ እንስሳት ሕክምና ባለሙያ ትዕዛዝ የጸረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶችን ለእንስሳት መስጠት እና የፀረ- ተኅዋስያን መድኃኒቶች ቅሪት ያለበትን የእንስሳት ተዋፅኦ መመገብ፤ከዚህ በፊት ተወስዶ ስላዳነ ብቻ ተመሳሳይ መድኃኒቶችን ገዝቶ መጠቀም፤መድኃኒት ለማያስፈልጋቸው ወይም ሰውነታችን በተፈጥሮ ባለው ኃይል ሊቋቋማቸው ለሚችሉ ሕመሞች መድኃኒት መውሰድ፤የግልና የአካባቢ ንጽህናን አለመጠበቅ፤ትክክለኛ የመፈወስ አቅም የሌላቸውን መድኃኒቶች ሕጋዊ ካልሆኑ መድኃኒት ቤቶች ወይም ግለሰቦች ገዝቶ መውሰድ፤የጤና ባለሙያዎች የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶችን አለአግባብ እንዲያዙ መገፋፋት፤ጥቅም ላይ ያልዋሉ የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች ያለአግባብ በቆሻሻ መልክ መጣልና የመሳሰሉት ናቸው።

### ችግሩን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች

ይህንን ዓለምአቀፍ ችግር ለመግታትና ለመቆጣጠር የዓለም ጤና ድርጅት፤ የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት እና የዓለም የእንስሳት ጤና ድርጅት በመተባበር ዓለም አቀፍ የጸረ ተኅዋሲያን መድሃኒት መለመድ የመከላከልና የመቆጣጠር ስትራቴጂና ዕቅድ አውጥተው አባል አገሮች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው።

ኢትዮጵያም የጸረ ተኅዋስያን መድሃኒቶች መለመድ በሰው፤ በእንስሳትና አካባቢ ጤና እንዲሁም በኢኮኖሚ ላይ እያደረሰ ያለውን ችግር በመገንዘብ ስትራቴጂክ እቅድ በማውጣትና ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ሙያተኞችን ያካተተ አገራዊ አማካሪ ኮሚቴ በማዋቀር ባለፉት አስርት ዓመታት የጸረ-ተኅዋስያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎች በሰው፤ በእንስሳትና በአካባቢ ጤና ዘርፍ እየተሰሩ ይገኛሉ። ከነዚህም ስራዎች መካከልም ለሕብረተሰቡና ለጤና ባለሙያዎች ስለ ችግሩ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ በሆስፒታሎች የኢንፌክሽን ስርጭትን መቀነስ፣ በሰውና በእንስሳት አግባባዊ የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች አስተዛዘዝና አጠቃቀምን መተግበርና የተለያዩ ቅኝት ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ ይጠቀሳሉ።

በዚህም መሰረት ሀገር አቀፍ የፀረ-ተኅዋሲያን መድኃኒቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ቀን ዘንድሮ ለ12ተኛ ግዜ "የፀረ-ተኅዋሲያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነትን ማጠናከር! ("Strengthening public private partnership to combat Antimicrobial Resistance") በሚል መሪ ሀሳብ ሰኔ 7 ቀን 2016 ዓ.ም በተለያዩ ፕሮግራሞች ይከበራል።

### የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት

#### እንስሳት አርቢዎች

እንስሳት አርቢዎች እንስሳትን በአግባቡ መመገብ፣ ንፅሕናቸውን መጠበቅ እና ማስከተብ፣ የታመሙ እንስሳትን በባለሙያ ማስመርመር እና አስፈላጊ ሲሆንም በሽታው ወደሌሎች እንዳይተላለፍ ለብቻ ነጥሎ መንከባከብ፣ የፀረ-ተኅዋሲያን መድኃኒቶችን ለእንስሳት ጤና በባለሙያ ምክር ብቻ መጠቀም፣ ያለማቋረጥ፣ ያለሚጋራት፣ ከመጠን አስበልጦም ሆነ አሳንሶ አለመጠቀም፣ የሰው መድኃኒቶችን ለእንስሳት ወይም የእንስሳትን ለሰው አለመጠቀም፣ የፀረ-ተኅዋሲያን መድኃኒቶችን እየወሰዱ ያሉ እንስሳት ተዋፅኦ ለምግብነትም ሆነ ለገበያ አለማዋል፣ እንስሳው በጤና ባለሙያ ትእዛዝ መሠረት መድኃኒት ወስዶ ካልተሻለው በድጋሚ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ማማከር፤መድኃኒቶችን ከቀጥታ የፀሀይ ብርሃን፣ ሙቀት እና እርጥበት እንዲጠበቁ ማድረግ፣ የእንስሳት መድኃኒቶችን እና መኖ ሕጋዊ ፈቃድ ካላቸው ድርጅቶች ብቻ መግዛት ይጠበቅባቸዋል።

#### የሰውና የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች

ባለሙያዎች በጤና ተቋማት ኢንፌክሽንን መከላከል፤ፀረተኅዋሲያን መድኃኒቶችን አስፈላጊ ሲሆን ብቻ በሥርዓቱ በተቀመጠው መሠረት ማዘዝና ማደል፣ መድኃኒቶች አስፈላጊ የማይሆኑበትንና አስፈላጊ ሆኖ ሲታዘዝም ስለ ትክክለኛ አጠቃቀም ሕብረተሰቡን በተለያየ መንገድ ማስተማር፣ የበሽታና የፀረተኅዋሲያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ቅኝት ማካሄድና በውጤቱም መሰረት ተግባራዊ ማድረግ፣በየማሕበሮቻቸው አማካይነት በመካከሉና መቆጣጠሩ ሥራ መሳተፍ አለባቸው።

#### ፖሊሲ አውጪዎችና ተቆጣጣሪ አካላት

ፖሊሲ አውጪዎችና ተቆጣጣሪዎች የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣ መከለስ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል፤በየሴክተሩ ችግሩን የመካላከልና የመቆጣጠር ሥራ እቅዶች እንዲከተቱ ማድረግ፤የመድኃኒት አጠቃቀምንና የጸረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶችን መላመድ በተመለከተ ቅኝት ማካሄድ፤የኢንፌክሽን መከላከል ፕሮግራምን እና አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ቁጥጥርን ማጠናከር አለባቸው።

#### የትምህርትና ምርምር ተቋማት

የትምህርትና ምርምር ተቋማት ስለ ፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ መንስኤ፤ተጽእኖ መከላከልና መቆጣጠር በስርዓተ ትምህርት ማካተትና ማስተማር፤በተለያዩ ክበባትና መድረኮች በተጋባዥ እንግዳ ጭምር ተማሪዎች እንዲያውቁና ተማሪዎቹም በዙሪያቸው ያሉትን ማሳወቅ፣ ስለ ተላላፊ በሽታዎችና ጸረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች ምርምር ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል።

### ማጠቃለያ

የፀረ-ተኅዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መላመድን መከላከልና መቆጣጠር ለአንድ አካል ብቻ የምንተወው ሳይሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብን የሚጠይቅ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ